የመጋቢያን እና የመሪዎች ኮንፈረንስ

አዲስ አበባ

የካቲት 2016

# የእግዚአብሔር ልዩ ሐይል

J16 THE JOSHUA PROJECT

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

**በሬቨረንድ ኪንግስሊ ኤን አርምስትሮ**

## የእግዚአብሔር ሰው ነብዩ እና ኢዮርብዓም

## "አንተ ማድረግ ያለብህ የተለዩ ነገሮች አሉ"

### መግቢያ እና ማስታወሻ

**2 ነገሥት 22፡1**

ኢዮስያስ ሲነግሥ ዕድሜው ገና ስምንት ዓመት ነበር ፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ሠላሳ አንድ አመት ገዛ፡፡ እናቱም የባሶርት አገር፡ ሰው ፤የአዳያ ልጅ፡ ይዲዳ ነበረች፡፡

**300 + ዓመታት በፊት**

**1 ነገሥት 13፡1-6**

ኢዮርብዓም፡ መሥዋት ፡ ለማቅረብ ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ሳለ ፡ በእግዚአብሔር ቃል ታዝዞ፡ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ከይሁዳ ፡ ወደቤተል መጣ፡፡ መሠዊያውንም ፡ በ እግዚአብሔር ቃል ፡ በመቃወም እንዲህ አለ "አንተ፡ መሠዊያ ሆይ! እንግዲህ እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው ፡ "እንሆ ፥ኢዮስያስ የተባለ ፡ ለዳዊት ፡ ቤት ፡ ይወለዳል እርሱም ፡ አሁን ፡ እዚህ መሥዋዕት ፡ የሚያቀርቡትን ፡ የኮረብታ ፡ ማምለኪያ ፡ ካህናት ፡ በላይህ ይሰዋቸዋል፤ ሰዎችም ዐጥንት በአንተ ላይ ይነድዳል፡፡" በዚያች ለት ያ፡ የእግዚአብሔር፡ ሰው፥ እንዲህ ሲል ፡ ምልክት ሰጠ ፡ "እግዚአብሔር ፡ የሰጠው ምልክት ፥ "እንሆ መሠዊያው ይሰነጠቃል ፡ በላዩም ፡ ላይ ፡ ያለው ዐመድ ይፈስሳል" የሚል ነው፡፡

ንጉሱ፡ ኢዩርብዓምም፡ ያ የእግዚአብሔር ሰው በቤቴል መሠዊያ ላይ ጮኾ የተናገረውን ሲሰማ ፥እጁን ፡ መሠዊያው ካለበት በመዘርጋት "ያዙት"! አለ ፡ ነገር ግን ያች፡ የዘረጋት እጅ ፡ ደርቃ፡ ቀረች ፤ ሊመልሳትም ፡ አልቻለም እንዲሁም ፡ ያ ፡ የእግዚአብሔር ሰው፡ በእግዚአብሔር ቃል ተመርቶ፡ በሰጠው ምልክት መሠረት መሠዊያው ተሰነጠቀ፤ ዓመድም ፈሰሰ፡፡

ከዚያም ንጉሡ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፥ "እጄ፡ ወደቦታዋ፡ እንድትመለስ ፡ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ለምንልኝ፡ ጸልይኝም አለው፡፡ ስለዚህም የእግዚአብሔር ሰው እግዚአብሔርን ለመነ ፡ የንጉሱም ፡ እጅ፤ ወደቦታዋ፡ ተመለሰች፡ እንደ ቀድሞዋም ፡ ሆነች፡፡ ትንቢቱ የተነገረው ከክርስቶስ ፡ ልደት ፤ በፊት 931 አካባቢ ሲሆን ፡ ኢዮሲያስ የነገሰው ከክርስቶስ ፡ ልደት በፊት 627 አካባቢ ነው፡፡ በመሆኑም ትንቢቱ የተፈጸመው ከ300 አመታት ፡ በላይ በኋላ ነው፡፡

### የትውልዶች ፡ ታማኝነት

**ሕዝቂያስ** = "ማጠንከር "፥"መያዝ" ፥"መጀገን" ፥" ግምት" ተብሎ ሊተረጉምም፤ ይችላል

**ምናሴ** = "መርሳት" ማለት ነው

**አሞን** = አስተማሪ / ገንቢ ማለት ነው፡፡ በጥንቶ ግብፅ ፤ የታወቀ፡ ስያሜ፡ ሲሆን ትርጓሜውም "የተሰወረው" ማለት ነው ፡፡ አመንራ ራሱን የፈጠረ የገለጠ አምላክ ማለት ነው፡፡

**ኢዮስያስ** = "ያሕዌ የፈወሰው" ወይንም "ያሕዌ ይረዳል" ማለት ነው ፡፡

**ይዲዳ** = (የኢዮስያስ ፡ እናት) "የተወደደ" ማለት ነው፡፡

## የእግዚአብሔር ፡ ሰው፡ ነብዩ እና ኢዮርብዓም

1ነገሥት 13(ተንዳኝ ምንባብ 1ሳሙኤል 2፡27-36 ስሙ ፡ ያልተጠቀሰ ፡ የእግዚአብሔር ሰው ዔሊን ፡ አናገረው)

የ S. A S. መርህ (የብሪቲሽ አርሚ ስፔሻል ፎርስ = ስፔሻል ኤር ሰርቪስ)

( የእንግሊዝ ሰራዊት ልዩ ሐይል = ልዩ የአየር አገልግሎት)

"እኛ ፡ የተካንን ፡ ተጓዦች ነን ፤ ሁል ጌዜ ፡ ጥቂት ፡ አለፍ ብለን ፡ እንጓዛለን ፤ ብዙ ፡ ቁጡና አብረቅራቂ ባሕር

ባሻገር ፡ ካላ በበረዶ በተሸፈነ፡ ሰማያዊ ተራራም ፡ አልፈን፡ እነጓዛለን ፡፡"

### ቁልፍ መርሆች

1. ስም የለሽ፥ዝና የለሽ ፥ ቅርስ የለሽ
2. የተለየ መለእክት፥ የተለየ ኢላማ፥የተለየ ጌዜ
3. ምልአችን፡ ሰጠ

### የተነሱ ጉዳዬች

1. ቅናት
2. አዋቂ፡ የሚባሉ ፡ሰዎች ፡ ነገር፡ መጎንጎን ጀመሩ

# የልዩ ሐይል ምልመላ

## "አንተ ማድረግ ፤ ያለብህ፡ የተለዩ፡ ነገሮች ፡ አሉ"

### የእግዚአብሔር ፡ልዩ የአየር አገልግሎት

## ክፍል 2 ፊልጶስ

### ሐዋርያት 6፡3 - ከሰባቱ አንዱ

መልካም፡ ስም ያላቸው፥ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ፥በጥበብ የተሞሉ

በሐዋርያት ፊት ቀረቡ ፡ ፀልየው ፡ እጃቸውን ጫኑባቸው፡፡

**የሐዋርያት ሥራ 8፡1** ከሐዋርያት ፡ በቀር፡ ሁሉም ተበተኑ

**የሐዋርያት ሥራ 8፡4** ተበተኑ

**የሐዋርያት ሥራ 8፡5** ፊልጶስም ፡ ወደ ፡ ሰማሪያ ወረደ ፥ ክርስቶስን ሰበከላቸው፡፡

**የሐዋርያት ሥራ 8፡26** የጌታም መልአክ ፡ ፊልጶስም ተነሥተህ ፡ በደቡብ በኩል በሚወርደው ፡ በምድረበዳው ሂድ አለው እርሱም ተነስቶ ሂደ፡፡

**ቁጥር 37 እና 38** ድነትና ጥምቀት

**B የሐዋርያት ሥራ 8፡39** የጌታ መንፈስ ፡ፊልጶስም፡ ነጥቆ ወሰደው ፤ ጃንደረባውም ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አላየውም ፡ ሆኖም ደስ፡ እያለው ጉዞውን ፡ ቀጠለ

**ቁጥር 40** ተነጥቆ ፡ በአዛጦን ታየ ፡ በቂሳሪያ ፡ እና በሌሎች ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ ሰበከ

**-የሐዋርያት ፡ ሥራ 21፡ 8-10** ቡድኑን ፡ ተቀበለ፡አሳረፈ፡ አጋቦስንም ፡ ተቀበለው አስረዳው፡፡

ስለዚህ ምን ፡ መማር እንችላለን?

እግዚአብሔር የተለዩ ሰዎችን እያስነሳ ነው

1. ስምህን ፡ ማንም ፡ አያውቀውም
2. ይሔ ነው፡ የሚባል ታሪክና ፡ ቅርስ አይኖርህም
3. የተለየ መልእክት ፥የተለየ ጊዜ ፥የተለየ ኢላማ
4. በድንቅ እና ተአምር የሚያምንና የሚያገለግል
5. ለራሱ ክብር የማይወስድ፥ወደ ክርስቶስ የሚጠቆም
6. ድርጅቱ ይቀናበታል
7. የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ
8. የእግዚአብሔርን ሰዎች እና ነበያተን ተቀብሎ ፡ የሚያሳርፍ
9. ከጀርባ ፡ የሚሰራ
10. ከተለመዱ ፡ ደንቦች ፡ ውጭ የሚንቀሳቀስ

## ልዩ ሐይል ምልመላ

## " አንተ፡ ማድረግ ፡ ያለብህ፡ የተለዩ፡ ነገሮች አሉ

## የእግዚአብሔር ፡ ልዩ፡ የአየር፡ አገልግሎት

## ክፍል 3- ሐናኒያ

ደማስቆ፡- የሶርያ ፡ ዋና፡ ከተማ

- በአለማችን ፡ እድሜ ጠገብ ፡ ከሆኑ ፤ ከተሞች ፡ አንዱ ነው
- እንደ ዩሲፈስ፡ ከሆነ ደማስቆ ፡የተቆረቆረችው በሴሜ ፡ የልጅልጅ ፡በዑፅ ነው
- በአብርሐም ዘመን ፡ ተጠቅሷል
- ለኢየሩሳሊም ፡ በስተሰሜን ምስራቅ ፡ በ218 ኪሎ ሜትር ፡ ርቀት ላይ ይገኛል
- ደማስቆ የ jasmine ከተማ
- የሕዝብ ፤ ቁጥሯ በአሁኑ ጊዜ ከ 2.5 እስከ 5 ሚሊዮን ፡ ይገመታል
- በ1950 የሕዝቧ፡ ቁጥር 414000 ነበር
- በጥንቷ፡ ደማስቆ ሁለት ቀጥ ፡ያሉ አውራ ፡ ጎዳናዎች ፡ ነበሩ ፤ አንደኛው 1.5 ኪሎ ሜትር ፡ ሲሆን ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ፡ የተዘረጋ ነው ፤ ሌላኛው 1ኪሎ ሜትር ሲሆን ፡ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ የሚወስድ ነው፡፡
- በዙሪያዋ፡ ሮማዊያን ፡ በሰሩት 4.5 ኪሎ ሜትር ቅትር ተከባለች
- በጳውለስ ዘመን በግምት 50,000 አይሑድ ፡ በደማስቆ ይኖሩ ነበር
    - በከፉው፡ የሮም ንጉስ ኔሮ ዘመን ፥ 10, 000 አይሁድን ፡በሔርዶስ የኢስፓርት አዳራሽ ታርደዋል

**ሐናኒያ የደማስቆ ሰው ነበር**

**ሐዋርያት ሥራ 22፡12** "ሐናንያ... ሕግን ፡ በጥንቃቄ ፡ የሚጠብቅና ፡ በዚያ ፡ በሚኖሩት ፡ አይሁድ፡ ሁሉ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ የተከበረ ሰው ነበር፡፡"

- እርሱ ከኢየሩሳሊም ፡ የመጣ ስደተኛ ፡ አልነበረም
- የከማይቱን ፡ መግቢያና፡መውጫ ያውቅ ነበር
- በከተማይቱ ፡ ባሉ አይሁድ ዘንድ ፡ እጅግ ፡የተከበረ፡ ነበር
- ደቀመዝሙር የሚል ፡ ስያሜ ፡ ተሰጥቶታል
- ሆኖም ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያናግረው ፡ ነብይ ፡ እንደነበረ፡ ግልጥ ነው
- አንዳንድ የታሪክ ፡ አዋቂዎች ፡ ኢየሱስ ፡ ከላካቸው ፡ 70 ሰዎች፡ ውስጥ ነበረበት ፡ ይላሉ
- ከኪብሮን 2ኪሎ ሜትር ራቅ ብላ ፡ በምትገኘው ፡በኤልቴሮየሊስ እንደተሰዋ ፤ በአፈታሪክ ፡ ይነገራል
- በቃ፡ ስለዚህ ሰው የምናውቀው ፡ ይሄንኑ ፡ ብቻ ነው
- ባለትዳር ፡ እንደሆነ ፥ልጆች ፤ እንዳሉት ፡ አናውቅም
- ሥራው ፡ ምን እንደነበረ፡ አናውቅም
- በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ፡ ስለነበረው ፡ የአገልግሎት ፡ዘርፍ፡ አናውቅም
- ወዳጆቹን ፡ አናውቅም ፥ስለማህበራዊ ፡ ሕይወቱ አናውቅም ፥ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ ያለ ፡ አማኝ፤ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ እናውቃለን ፡፡

- ስሙ ፡ በመፅሐፍ ቅዱስ ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ አይገኝም ፡፡
- እግዚአብሔር ለምን መረጠው ? እግዜአብሔር ፡ የማንንም ፡ አገልግሎት ፡ ሳይጠቀም ፡ በተአምራት ፡ ለምን አልፈወሰውም?
- በእርሱ ፡ የተፃፈ ፡ ወይንም ፡ ስለእርሱ ፡ ገድል ፡ የተፃፈ፡ አንድም ፡ መፅሐፍ ፡ ስለምን ፡ አልተገኘም?
- ወንጌልን ይዞ፡ ወደ አሕዛብ የገባውን ፡ አብዛኛውን ፡ የአዲስ ፡ ኪዳን ፡ መልዕክትን ፡ የፃፈውን ፥በምድር ላይ ፡ ተወዳዳሪ የሌለው ፡ ሚሲዮናዊ ፡ ያስማራው ፡ እርሱ ፡ አይደለምን ?

አናንያ ፡ ተአምራዊ ፤ ነገሮችን ፡ ያከናወነ፡ ተራ ፡ ሰው ነበረ፡፡ አንዳች ፡ የተለየ ታሪክ ፥ዝና ፥ችሎታም ፥አገልግሎት ያልነበረው ፥ በእግዚአብሔረ ልዩ ሐይል ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ የታመነ ፡ ሰው፡ ነበር፡፡

# የልዩ ሐይል ምልመላ

## " አንተ፡ ማድረግ ፡ ያለብህ፡ ልዩ፡ ነገሮች አሉ"

## ክፍል 4- ቆርኖሊዮስ

**ቆሮኖሊዮስ** - መቶ አለቃው

ሐዋርያት ፡ ሥራ 10 ፥በተጨማሪም ኋላ በመስቀሉ ፊትም ተገኝቶ ይሆናል

- አንዳንድ ፡ ምሑራን ፡ እና ፡ የስነመለኮት ፡ ሰዎች ፡ በማርቆስ 15 የክርስቶስን፡ መስቀል ፡ ቆሞ፡ የተመለከተው ፡ መቶ ፡ አለቃ ፡ ይሔው ፡ ሰው፡ እንደሆነ፡ ያስባሉ፡፡ ይሕ፡ መቶ አለቃ " ይህ ፡ ሰው ፡ በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ነበር" ያለው ፡ ሰው፡ ነው፡፡
- ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ "ይህ ፡ ሰው ፡ በሉቃስ 7፡1-10 ላይ ፡ አገልጋዩ፡ የተፈወሰለት ፡ የመቶ አለቃ ፡ ነው ፡ ይላሉ፡፡ ". . . ሕዝባችንን ፡ ይወድዳል ፤ ምኩራባችንንም ያሠራልን እርሱ ነው" የተባለለት ፡ እርሱ ፡ ነው ይላሉ ፡፡

## ስለእርሱ፡ የምናውቀው ፡ ምንድን ነው?

- **በቅርብ ፡ የሚያውቁት ሰዎች ፡ ይበልጡኑ ፡ ያከበሩት ፡ ሰው፡ ነው**
- **ዘላቂ ፡ ወዳጅነትን፡ ለመመስረት ፡ ዋጋ፡ የከፈለ ፡ ሰው ፡ ነው**
- **የእግዚአብሔርን ፡ ሐብት ፡ በባለአደራነት ፡ የያዘ ፥በቸርነት የሚሰጥ ፡ሰው ነበረ**
- **የፀሎት ሰው ፡ ነበረ**

1. የሮማውያን ፡ የመቶ አለቃ ነበር ( ከ5,000-6,000) ወታደሮች ፡ በያዘ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ የመቶ ፡ ወታደሮች ፡ አለቃ ፡ ነበረ
2. በመሆኑም ፤ ትልቅ ፡ ብቃት፥እና በዳጉስ ፡ ያለ ፡ ደሞዝ ፥ የተከበረ ፡ ስፍራ ያለው ፡ ሰው፡ ነበረ፡፡
3. ጣልያናዊ ፡ ነበረ
4. የተሰጠ፡ የሐይማኖት ፡ ሰው ፥አብዝቶ ፡ የሚፀልይና ፡ የሚፃም ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡፡
5. ለድሆች ፡ ምጽዋዕት ፡ የሚሰጥ ሩሕሩሕ ፡ ሰው ፡ ነበረ፡፡
6. ለመንፈስ ቅዱስ ፡ የነቃ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ የሚያናግረውን ፡ መልአክ ፡ የለየ ፡ ነበረ ፡
7. ፈጥኖ ፡ የሚታዘዝ ነበር
8. በአካባቢው ፡ ያሉትን እግዚአብሔርን ፡ የሚከተሉትን ፡ ሰዎች፡ ያውቃቸዋል
9. በጴጥሮስ እግር ፡ ስር ፡ የወደቀ እጅግ ፡ ትሁት ፡ ሰው ነበረ
10. በስራውም ፡ ስፍራ ፡ በመንፈሳዊው ፡ አተያይ ፡ የመሪነት ፡ ስፍራ፡ ነበረው
11. እግዚአብሔር ፡ የሚለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ፡ ለመስማት ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ነበር
12. መንፈስ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብሎ ፡ በልሳን ፡ የተናገረ ፡ ሰው ፡ ነበር
13. ኋላም ፡ የሙሴን፡ ጥምቀት ፡ ወስዶ ፡ ነበር

ከዚህ ፡ ኩነት ፡ የተነሳ ፡ የአሕዛብ ፡ አለም ፡ ለወንጌል ፡ ተከፈተ ፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ተከታይ ፡ ባይሆንም እንኳን ፡ የልዩ ሐይል ፡ አባል ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡በእግዚአብሔር ፡የተመረጠ ፡ ነበር፡፡ የእግዚአብሕር ተከታዮች ፡ ይሆናሉ ፤ ብለን ፡ ፈፅሞ፡ ባልጠበቅናቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፤ እግዚአብሔር ፡ እጁን ፡ ይጭናል ፡፡"

# የልዩ ሐይል ምልመላ

## " አንተ፡ ማድረግ ፡ ያለብህ፡ ልዩ፡ ነገሮች አሉ"

## የእግዚ አብሔር ፡ ልዩ ፡ ሐይል - ልዩ የአየር ፡ አገልግሎት

## ክፍል 5- ረዓብ

- **<u>ኢያሱ 2፡1</u>** ጋለሞታዋ ረዓብ
- **<u>ማቴዎስ 1፡5</u>** ሰልሞን ቦዔዝን ፡ ከረዓብ ፡ ወለደ
- **<u>ዕብራዊያን 11፡31</u>** ጋለሞታይቱ ረዓብ በእምነት
- **<u>ያዕቆብ 2፡25</u>** ጋለሞታይቱ ረዓብ ፡ በሥራ ጸደቀች

### 1. በከተማው ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ የምትኖር ፡ መበለት ፡ ነበረች

- የረዓብ ፡ ቤት በውጭው ፡ በር ፡ ላይ ፡ ነበር
- ስለዚህም ፡ ቀድሞውኑም ፡ የውጪ፡ ሰው ፡ ነበረች
- ቁጥር 15 ፥18 እና 21 መበለቲቱ
- ማንም ፡ ሊያይ ፡ ያልቻለውን ፡ ማየት ችላ ነበር
- እርሷ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ተመለከተች -ሌሎች ፡ በሙሉ ወደ ውስጥ ፡ ተመለከቱ
- ለነገ ፡ አእምሮዋን ፡ በተስፋ ፡ ሞላችው
- ተአምራትን ፡ ስለሚሰራው፥የተረገጡትን ፡ እና ፡ የተጕዱቱን ፡ ስለሚያስጥል ፡ አምላክ ፡ አለመች

### 2. በመስኮቱ ፡ላይ ፡ ገመድ ፡ አንጠለጠለች

- ቲክቫ - ገመድ - ተስፋ
- **"ካቫ"** ከሚል ፤ ቃል ፡ የመጣ ፡ ሲሆን ፡ ትር ገሜውም ፡ በጋራ ማሰር ፥መሰብሰብ ፥መጠባበቅ ፡ እና መጠበቅ ማለት ነው
- ኢያሱ 2፡17-18 እና 21 - በቀይ ክር የተገመደ ገመድ( ከሩት 1፡11-13 ፥ ኤርምስ 29፡11 ፥ ሆሴ 21፡5 ፥ዘካርያስ 9፡11-13 ጋር ያነፃፅሩ)

### 3. ለሰላዩች መልእክት ነበራት

- **<u>ያቆብ 2፡25</u>** ጋለሞታዋ ረዓብ መልእክተኞችን ፤ ተቀብላ ፡ በሌላ ፡ መንገድ በሰደደቻቸው ፡ ጊዜ ፡ በሥራ ፡ አልፀደቀችምን?
- ያዕቆብ ለትምሕርቱ ፡ ምሳሌ ፡ይሆንለት ዘንድ ፡ ከብሉይ ፡ ኪዳን ፡ የመረጣቸው ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ የእምነት ፡ አባት ፡ የሆነውን ፡ አብርሐምንና ረዓብን እንደሆነ ፡ ልብ በሉ፡፡
- ኢያሱ 2፡16 ከጌታ የሆነውን ፡ መልክት ፡ ነገረቻቸው ፤ ሕወታቸውንም ፡ ያተረፈውን ፡ ግልፅ ፡ መመሪያ፡ ሰጠቻቸው ፡፡ የነርሱን ፡ መልክት የያዘችው ፡ እርሷ ፡ ነበረች ፡፡

# የልዩ ሐይል ምልመላ

## “ አንተ፡ ማድረግ ፡ ያለብህ፡ ልዩ፡ ነገሮች አሉ”

## <u>ክፍል 6- አባብ</u>

አቦብ ፡ የተጠቀሰው ፡ በሁለት፡ ቁጥሮች ፡ ብቻ ፡ ነው

1. **ዘ'ኁቅ 10፡29** ሙሴ አባብን “ከእኛ ጋር እንሔድ አለው”
2. **መሳፍንት 4፡11** የአባብ ልጆች ፡ ከሆኑ ቀናዊው ሔቤር

- ኤሳው የአባብ ፡ አያት ነበረ ( የኤሳው ፡ ሚስት ቤስሞት ራጉኤልን ወለደች )
- **መሳፍንት 1፡16** የቄናዊው ፡ የሙሴ ዐማት ፡ ዝርያዎች ፡ ወጡ

ዘኍልቁ 10

ቁጥር 29 እንሆ እግዚአብሔር (ያህዌ) “እሰጣችኋለሁ” ወዳለን ፡ ምድር ፡ ጉዞ ፡ ጀምረናል ፤ “ከእኛ ጋር ሂድ፡፡

“በመልካም ሁኔታ እናኖርሀለን”

ቁጥር 30 “አልሔድም” ÷ “ወደ አገሬና ወደ ወገኖቼ ፡ ተመልሼ እሄዳለው”

ቁጥር 31 “እባክህ ፡ አትለየን - ዐይናችን ፡ ትሆናለህ”

ቁጥር 32 ከበረከቱ ተካፋይ ትሆናለህ

ከመሳፍንት 1 እና 4 እንደምናየው ፡ አባብ ፡ አብሯቸው ፡ ሔዷዋል ፡፡

ስለዚህም እኛም አንዳንድ ጌዜ

- ከሌላው ፡ ራዕይ ፡ ጋር ፡ መሮጥ ፡ ይኖርብናል
- ላቅ ፡ ያለው ፡ ጥሪ ፡ አካል ፡ መሆን፡ ይኖርብናል
- የቡድን ፡ አባል ፡ መሆን ፤ ይኖርብናል
- በፊትህ ፡ ያለው ፡ ክፍተት ፡ ለአንተ ፡ ጥሪ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡፤

**ቆሮንጦስ 12፡8** የአካል ብልቶች ሁሉ አስፈላጊ ናቸው
**ኤፌሶን 4፡ 11-13** ቅዱሳንን ማነፅ
**ገላቲያ 6፡2** አንዱ የሌላውን ፡ሸክም ፡ ይሸከም

የእንግሊዝ ፡ ንጉሳዊ ፡ አየር ፡ ሐይል 192 በስራ ላይ ፡ ያሉ ፡ ጀቶች ፡ ሲኖሩት ፡ የሰራተኖቹ ፡ ቁጥር ፡ ደግሞ 33,000 ፤ በዚህም ፡ መሰረት ፡ ለአንድ ፡ ጀት 170 ሰራተኞች ተመድበለታል ማለት ነው ፡፡

## በሐዋርያት 1( አንድ) የሚገኝ ፡ አስደናቂ ፡ ቃል

- 120 ሰዎች ፡ በሰገነቱ ፡ ነበሩ

- ይሁዳን ፡ ለመተካት ፡ ፈለጉ ፡፡ ከበርሲያን ና ከማቴያስ አንዱን ፡ መረጡ፡፡ ቁጥር 22 እንደሚነግረን እነርሱን ፤ እጩ ፡ ያቀረቡበት መስፈርት "ከዮሐንስ ፡ ጥምቀት ጀምሮ ኢየሱስ ፡ ከእኛ ተለይቶ ፡ እስካረገበት ፡ ድረስ ፡ የነበረ" የሚል ነው፡፡

**ሮሜ 16፡ 3-5** ጳውሎስ ፡ ሰላምታ ፡ የላከላቸው ፡ ግለሰቦችና ፡ ቡድኖች 27(ሃያ ሰባት) ይሆናሉ
**ሲቃስ 5፡ 17-26** ሽባውን ፡ ሰው ፡ ወዳጆቹ ተሸከሙት ፤ ኢየሱስም ፡ እምነታቸውን ፡ ተመለከተ ፡፡
**ሉቃስ 5፡ 1-11** መረባችሁን ጣሉ ፤ የቡድን ፡ አስፈላጊነትን ፡ ያሳያል

ታዋቂነት ፡ የለም ፥ታሪክ፡ የለም ፥ ቅርስ፡ የለም ፡ ለጌታ ግን ታማኝነት አለ ፡፡

## <u>በ2 ነገሥት 1፡ 10-15 የምናገኘውን ኢዮናዳብን አስታውሱ</u>

- የሬካብ ልጅ ነበረ ፡ ነገር ግን ፡ ከየት ነው ፡ የመጡት?
- **ዘጸአት 2፡21** ሙሴ የሚዲያማዊውን፡ ካሕን የዮቶርን ፡ ልጅ ፡ አገባ
- **ዘኁልቅ 10፡48** ሙሴ ፡ የአማቹን ፡ ልጅ፤ አባብን ፡ አብሮአቸው ፡ እንዲሄድ ፤ ጠየቀው
- **መሳፍንት 1፡ 16** የቄናዊው ፡ የሙሴ ሀማት ዝርያዎች ከይሁዳ ፡ ሰዎች ጋር ፡ በመሆን ፡ ከባለ ፡ ዘንባባዋ

  ከተማ ፡ ከኢያሪኮ ወጡ፡፡

- **መሳፍንት 4፡11** በዚህም ፡ ክፍል ደግመኛ ፡ እናገኛቸዋለን - ከቄናዊያን ራሳቸውን ፡ ይለያሉ፡፡
- **መሳፍንት 4፡17** የሄቤር ፡ ሚስት ፡ ኢያዔል የጠላት ስራዎች ፡ አዛዥ፡ የነበረውን ፡ ሲሣራን ፡ ገደለች
- **1ሳሙኤል 15፡6** ሳኦል ፡ አማሌቃዊያንን ፡ እንዲያጠፉ ፡ በታዘዘ ፡ ወቅት ፥ ቄናዊያን ከመካከላቸው ፡ እንዲወጡ ፡ ጠየቃቸው፡፡
- **1 ዜና 2፡ 55** እነዚህ ከሬካብ ፡ ቤት ፡ አባት ፡ ከሐማተ ፡ የመጡ ፡ ቄናውያን ፡ ናቸው ፡፡
- **2 ነገሥት 10፡15** ኢዩ ሰረገላውን ፡ አቆመ ፡ እጁን ፡ ሰጠው

  <u>ኤርምያስ 35፡ 18-19</u>

ሬካባዊያንን ፡ ወደ መቅደስ ፡ እንዲያመጣቸው ፡ እግዚአብሔረ ፡ ኤርሚያስን አዘዘው፡፡ የወይን ጠጅ ፡ አቀረበላቸው ፤ ለመጠጣት ፈቃደኞች ፡ አልነበሩም ፡፡ ወይን ጠጅ ፡ አትጠጡ ፥ ወይን አትትከሉ ፥ ዘር አትዝሩ፡፡

**ቁጥር 18** የአባታችሁን ፡ የኢዮናዳብን ፡ ትዕዛዝ ፡ ስለ ጠበቃችሁ ፥ መመሪያውን ፤ ስለተከተላችሁ፥ያዘዘችሁንም ፡ ሁሉ ፡ ስለፈፀማችሁ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ጌታ ፡ እግዜአብሔር እንዲህ ይላል ፥ከሬካብ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮናዳብ ወገን ፡ የሚያገለግለኝ ፡ ሰው ፡ ለዘላለም ፡ አይታጣም ፡፡

**ነህምያ 3፡14** የርሱ ፡ ልጅ ፡ ከስደት ፡ ተመለሸ ነበር ፤ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ፡ መልስ ፡ በመገንባት ፡ ስራ ፡ላይ ተሳተፈ

## የልዩ ሐይል ምልመላ

## " አንተ፡ ማድረግ ፡ ያለብህ፡ ልዩ፡ ነገሮች አሉ"

## ከፍል 7- ካሌብ

አንዳንድ ፡ ግዜ ፡ ለአምልኮ ፡ እንጠራለን ፤ ደፍሬ ፡ ልናገርና ፡ አንዳንድ ጊዜ ፡ አምልኮ ፡ አይበቃም !

**ማቴዎስ 14፡33** በጀልባ ውስጥ የነበሩት ፡ ደቀመዛሙርት ፡ ኢየሱስን ፡ አመለኩት ፤ወደ አምልኮ ፡ የገቡት ግን ጴጥሮስ ፡ ትልቅ የእምነት ፡ እርምጃ ፡ ወስዶ ፡ ከጀልባው ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ነው።

- በጥንታዊ ፡ የአይሁድ ፡ ባሕል ፡ ልብስን ፡ መቅደድ ፡ የጉዳት ፥የሐዘን ፥ የዋይታ ምልክት ፡ ነው ፡ በመሆኑም ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ወደ ኋላ ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ የሚያስቡት ነው። ከዚህ ፡ ያለፈ ፡ ነገረ ፡ የለም
- ለምሳሌ

- **ዘፍትረት 37፡29** ሮቢል ፡ ወደ ውሐው ፤ጉድጎድ ፡ ተመለሰ ፡የዮሴፍን ፡ ባጣው ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ
- **ዘፍትረት 37፡ 34** ውድ ፡ ልጁ ፡ የሴፍ እንደሞተ ፡ ባሰበ ፡ ጌዜ ፡ ያቆብ ልብሱን ቀደደ
- **2 ሳሙኤል 1፡ 11-12** ሳኦልና ፡ ዮናታን ፡ መሞታቸውን ፡ ሲሰሙ ፡ ዳዊት ፡ ልብሱን ቀደደ
- **ኢዮብ 1፤20** ቤተሰቡ እንዳለቀ ፡ በሰማ ፡ ጌዜ ፡ ኢዮብ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ
- **አስቴር 4፡1** ሐማ ፡ አይሁድን ፡ ሊያስጨርስ ፡ ማሴሩን ፡ ሲሰማ ፡ መርደኪዮስ - ልብሱን ቀደደ
- **1 ነገሥት 21፡27** ኤልያስ ፡ የጌታኝ ቃል ፡ በነገረው ፡ ጊዜ ፡ አካብ ፡ ልብሱን ፡ቀደደ

**ዘሌዋዊያን 21፡ 10** ልብሱን ፡ ለመቅደድ ፡ የማይፈቀድለት ፡ ብቸኛው ፤ ሰው ፡ ሊቀካሕኑ ፡ ብቻ ፡ ነበር፤ ይሕም ፡ አስገራሚ ነው።

**አዩኤል 2፡13** ይሕ ፡ ሐዘን ፡ የውስጥ ፡ መሆን ፤ እንዳለበት ፡ ተናገረ፥

"ልባችሁን ፡ አንጂ ፤ ልብሳችሁን ፡ አትቅደዱ፤ወደ ፡ አምላካችሁ ፡ ወደ፤ እግዚአብሔር ፡ ተመለሱ ፤ እርሱ ፡ መሀሪና ርኅሩኅ ፡ ቁጣው የዘገየና ፡ ፍቅሩ የበዛ ፤ ከፉ ነገርን ከማምጣት ፡ የሚታገስ ነውና ።"

## 1. ካሌብ

**ዘኁልቅ 14፡ 5 እና 6** "ከዚያም ሙሴና ፡ አሮን ፡ እዚያ ፡ በተሰበሰቡት ፡ በመላው ፡እስራኤላዊያን ፡ ማኅበር ፡ ፊት በግንባራቸው ፡ ተደፉ ፡ ምድሪቱን ፡ ከሰለሉት መካከል ፤ የነበሩት ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱና ፡ የዩፍኒ ፡ ልጅ ፡ ካሌብ ፡ **ልብሳቸውን ፡ ቀደዱ"**

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ለአምልኮ ፡ እንጠራለን ፤ ደፍሬ ፡ ልናገርና ፡ አንዳንድ ፡ ጌዜ ፡ አምልኮ ፡ አይበቃም !

**ማቴዎስ 14፡33** በጀልባው ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ደቀመዛሙርት ፡ ኢየሱስን ፡ አመለኩት ፤ ወደ አምልኮ የገቡት ግን ፡ ጴጥሮስ ፡ ትልቅ የእምነት ፡ እርምጃ ፡ ወሰወዶ ፡ ከጀልባው ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

በዙህ ስፍራ ቁልፍ ቃል "ምድሪቱን ፡ ከሰለሏት ፡ መካከል" የሚለው ነው፡፡ሙሴ እና ፡ አሮን ፡ ወደ ፡ከነአን ፡ አልገቡም ፡፡ ጀሸዋና ፡ ካሌብ ፤ግን ፡ ገብተዋል ፡ እነርሱ ፡ የተለዩ፡ ስለነበሩ ፡ "ልብሳቸውን ፡ ቀደዱ"

- **ካሌብን ተመልከቱት**

**ዘዳግም 1፡36** "ከካሌብ ፡ በስተቀር"

**ዘሁልቅ 14፡24** "የተለየ መንፈስ"

**ኢያሱ 14፡ 6-12** "ይህችን ፡ ኮረብታማ ፡ አገር ፡ ስጠኝ "

## የልዩ ሐይል አባል

### 2 ኤልሳእ

**2 ነገሥት 2፡11-12** ኤልሳእ ኤልያስ ወደ ሰማይ ሊያርግ ሲያይ ልብሱን ከሁለት **ቦታ ቀደደው**

በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ቁልፉ ፡ ያለው ቁጥር 10 ላይ ነው ፤ "አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ጠይቀሀል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እኔ ፤ ከአንተ ፡ ስወሰድ ፡ ብታየኝ ፡ እንዳልከው ፡ ይሆናል ፤አለዚያ ግን ፡ አይሆንም" አለው ፡፡

በመሆኑም ፡ የኤልሳእ ፡ የልብስ ፡ መቀደድ ፡ የአገልግሎት ፡ ዝግጅት ፡ ነው፡፤ ጌታ እንደጠራው ፡ የኤልሳ ፤ ቅባት ፤ እጥፍ ፡ ሆኖ ፡ በርሱ ፡ እንደመጣ ፡ አሁን ፡ ተረድቷል

**2 ነገሥት 5፡8** ኤልሳእ የእስራኤል ንጉስ ፤ ልብሱን ፡መቅደዱን ፡ በሰማ ፡ ጌዜ ፡ እንዲህ ሲል ላከበት ፤ ልብስህን ለምን ቀደድህ?

ሰውዬው ፡ ወደ እኔ ይምጣ ፤ ከዚያም ፤ በእስራኤል ፡ ነብይ ፡ መኖሩን ፡ ያውቃል

## የልዩ ሐይል አባል

### 3. ጳውሎስ እና ባርናባስ

**ሐዋርያት ፡ ሥራ 14፡14** ሐዋርያቱ ፡ በርናባስና ፡ ጳውሎስ ፡ ይህን ፡ በሰሙ ጌዜ ፡ ልብሳቸውን ቀድደው ፡ወደ ሕዝቡ ሮጡ ፤ ድምጻቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፤ እንዲህ አሉ ፡ እኛም ፤ እኮ እንደናንተው ፤ ሰው ነን!

ቁልፉ ፡ ቃል ፡ ያለው ፡ ቁጥር 9 ላይ ነው

"ጳውሎስም ፡ ወደርሱ ፡ ትኩር ፡ ብሎ ፡ተመለከተና፡ ለመዳን ፡ እምነት ፡ እንዳለው ፡ ባየ ፡ ጌዜ"

## የልዩ ሐይል አባል